PANORAMA # XXI

የትዝብት አድማስ

ሚያዚያ 2000 ዓም

## <u>የሠለጠነ የሰው ኃይል</u>

ምናልባት በአንድ እጅ ጣቶች ሊቆጠሩ ከሚችሉት ሀገሮች በስተቀር÷ በአፍሪካ ውስጥ ከአምሳና ስድሳ ዓመታት በፊት ዩኒቨርሲቲና የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት የነበራት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ እንደነበረች የሚካድ አይሆንም፡፡ እንዲያውም ከራሷ አልፋ ተርፋ ገና በቅኝ ግዛት የነበሩትን የአፍሪካ ሀገሮች ተማሪዎችንም ጭምር ሳይቀር የነፃ ትምሕርት ዕድል በመስጠት አሰልጥና ትልክ እንደነበረ ሁሉም የሚያውቀው ነው፡፡ በጊዜው የነበሩት ልዩ ልዩ የትምሕርት ተቋማትም የሀገሪቱን የዕድገትና የልማት ፍላጎት ሊያሟሉ ይችላሉ የተባሉትን የሰው ኃይላት እያሠለጠኑ በማውጣት ሲጫወትቱ የነበረው ሚና ዛሬ እንደፋና ወጊ ሊቆጠር ይችላል፡፡ ሀገርን ከድህነት÷ ከራሀብ÷ ከችግር÷ ከኋላ ቀርነት ለማውጣት ከተፈለገ መቸም የሠለጠነ የሰው ኃይል በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ ማንም አይስተውም ፡፡ በመሆኑም ከከፍተኛ የትምህርት መስጫ ማዕከሎች ሠልጥነው የወጡት ምሁራን÷ በህክምና÷ በርሻ÷ በህግ÷ በመሀዲስነት÷ በቴክኒክና በልዩ ልዩ ሙያ ውስጥ ተሰማራተው ሲያገለግሉ እንደነበር ዛሬ አስተዋይ ኅሊና ያለው ሁሉ የሚያስታውሰው ነው፡፡ የጀት አይሮፕላኖችን በማብረር በአፍሪካ ደረጃ ቀደምትነትን በመያዝ አድናቆትን ያተረፉት የኢትዮጵያ አየር ኃይልና የአየር መንገድ ፓይለቶችን አስደናቂ ችሎታ ማን ሊረሳው ይችላል? የኢትዮጵያን የመከላካያ ኃይል መኮንኖችን በጥራት እያስለጠኑ ሲያስመረቁ የነበረቱን ወታደራዊ ተቋማት ማለት÷ የሐረር ጦር አካዳሚ÷ የአየር ኃይል አካዳሚና የአባዲና ፖሊስ ኮሌጅን አገልግሎትና ወረታ ማን ይዘነጋዋል? ይህንን እንዲያው እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ተፈልጎ ነው እንጅ÷ በተለያዩ የሞያ መስኮች ተሰማርተው የነበሩት ባለሙያዎች÷ ለሀገራቸው ያበረከቱት አገልግሎት ግምቱን መተመን የሚቻል አልነበረም፡፡ የእኛ ነገር መቸም በነበር ብቻ መነገር ሆኖ ቀርቷል፡፡ አለመታደል ሆኖብነ !

የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት የተመሰረቱትና ባለሙያዎቹም የሠለጠኑት÷ ደሀው ገበሬና ሠራተኛ በከፈለው ግብር ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ግብር ከፋይ÷ በተለይም ገበሬውና ሠራተኛው÷ ይህንን የሚያደርገው/ያደረገው÷ ከዕለት ጉርሱ ከዓመት ልብሱ እየተነጠቀ ነበር፡፡ የድሀው ገበሬና የሠራተኛው ዓላማ÷ <u>ተምረው ያሳልፉልኛል</u> የሚል ነበር፡፡ አሁንም ያው ነው፡፡ የትምህርትም ዓይነተኛ ዓላማና ግብ ያው የሰውን ልጅ ኑሮና ሕይወት ወደ መልካም ሁኔታና ወደ ተሻለ የዕድገት ደረጃ መለወጥ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ገበሬ የኑሮ ሁኔታ ተለውጧል ባይባልም÷ ከአፉ እየተነጠቀ ለትምህርት ፕሮግራም

የዋለው ገንዘብ ደግሞ ሁሉም እንዲያው በከንቱ ፈሰሷል ማለት ያስቸግራል፡፡ መንገድ ተሰርቶለት፣ መብራት ገብቶለት፣ ንፁህ ውሃ ቀርቦለት፥ በየአቅራቢያው ትምህርት ቤት ተከፍቶለት፥ የጤና ጣቢያዎች ተቋቁመውለት የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ነዋሪ ዜጋ ህይወት ለመለወጥ ተችሏል ማለት ግን አንችልም፡፡ እራሳችንን ካላተልልን በስተቀር! በመሆኑም፥ የትምህርት መስፋፋትና የሠለጠነ የሰው ኃይል ማምረት ተቀዳሚና ዓይነተኛ ዓላማ፥ የሀገሪቱን ዜጎች ኑሮ መለወጥና የተሻለ ሕይወት እንዲመራ መድረግ መሆኑ ባይካድም፥ የሀገራችን የገጠር ነዋሪ ግን አሁንም ያው በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ከነበረው ህይወት ተለይቶ የሚታይ አለሆነም፡፡

የኢትዮጵያ ጉዳይ በሁለንተናዊ ገፅታው "አድሮ ጥጃ" ከመሆን አላላፈም፡፡ የትምህርት ተቋማት ብዛት፥ የተማረው ዜጋ መበርከት ዋናው ጥቅሙ፥ የአንድን ሀገር ዜጋ የኑሮ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነበር ፡፡ ይህ በሀገራችን እስካሁን አለተከሰተም፡፡ እንዲያውም በአያሌ መልኩ ሲታይ፥ወደ ከፋ ሁኔታ ተለውጧል፡፡ ምንም እንኳን በሀገራችን ለአለፉት ሠላሳ ሰባት ዓመታት ሁለት የተለያዩ ፈጣንና እጅግ ፅንፈኛ የሆኑ ብሎም፥ አንዱ ሌላውን የሚፃረር ለውጦች ቢካሄዱም፥ በኢትዮጵያ ብሄራዊ የኢኮኖሚ ጠቅላላ ድምር ውጤትም ሆነ፥ የዜጎቿ የነፍስ-ወከፍ ገቢ ምንም ያህል ያስገኘው ለውጥ የለም፡፡ በሽታው፥ ረሀቡ፥ ድኅነቱ፥ የሰላም ዕጦቱ፥ አለመረጋጋቱ፥ የትምህርቱ ደረጃ ዝቅ ማለቱ ወዘተ.. የዛሬ ሠላሳና አርባ ዓመታት ከነበረው ሁኔታ በሚያስከፋና በሚያስደነግጥ መልኩ ብሷል እንጅ አልተሻሻለም፡፡ በኢትዮጵያ የተፈራረቁት የደርግ ሶሻሊዝም ይሁን የወያኔ የጎሳ ፌደሬሽን ያስከተሉትን ብሄራዊ ጥፋት ሕዝቡ ስለሚያውቀው መዘርዘር የሚያስፈልገን አይመስለንም፡፡

ለአንድ ሀገር ዕድገትና ሥልጣኔ የሚያስፈልጉ ሁለት ዓበይት ጉዳዮች፥ ማለት የማኅበራዊ ስር ነቀል ለውጥና የሰለጠነ የሰው ኃይል ጉልበት ኢትዮጵያ አላጣችም ነበር፡፡ ነገር ግን ሁለቱም ተዋኅደውና ተጣምረው የሀገሪቱን መሠረታዊ ችግሮች ለመፍታት አልቻሉም፡፡ እስከ ዛሬ! ሁል ጊዜ "አድሮ ጥጃ"፥ ዘለዓለም ወደ ህይወት ሳይሆን፥ ወደ ከርሰ-መቃብር መውረድ ሆኗል ህይወታችን፡፡ እንዲያውም አንዱ በሌላው ላይ በመዝመት በአጥፊና ጠፊ ደረጃ ሲሰለፉ ነበር የታዩት፡፡ "ዓቢዮት ልጇን ትበላለች" ሆነና፥ ምሁራኑ የዓቢዮቱን አካሄድና አቅጣጫ በሚገባ ተረድተውና ተዘጋጅተው ለመምራት ዕድል አልነበራቸውም፡፡ ሁለቱንም የሀገር ጠቃሚ ጉዳዮች ጠቀሜታቸውን የሚያሳዩበትን ሁኔታ ለመግለፅ ሳይችሉ ቀርተዋል፡፡ ሁለቱም፥ ማለት አብዮቱና ምሁራኑ ድርና ማግ ሆነው ሰርተው ቢሆን ኖሮ፥ ከሠላሳ ሰባት ዓመታት በኋላና ያ ሁሉ መሥዋዕት ተከፍሎ፥ ዛሬ ሀገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ በጭራሽ መገኘት አልነበረባትም ነበር፡፡ እንዲያውም ይባስ ተብሎ፥ ልማቱና ዕድገቱ መምጣቱ ቀርቶ፥ እራሷ ሀገሪቱ እንኳን ዛሬ በህልውና ደረጃ በመሞትና በሽረት መካከል ትገኛለች፡፡ ይህም በመሆኑ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፥ "ጽድቁ ቀርቶብኝ በወግ በኮነነኝ"፥ ማለትም፥ ልማቱ ቀርቶብኝ ሀገሬ በዳነችልኝ ለማለት ተገድዷል፡፡ አሳዛኝ እንቆቅልሹና እስካሁንም መፍቻ ያልተገኘለት አዚም፥ ኢትዮጵያ ሁሉንም ሳታጣ አንዱንም አለማግኘቷ ነው፡፡

*ምሁሮቿም ሆኑ ዜጎቿ እንደ ባቢሎን ግንብ ሰሪዎች መስማማት፥ መደማመጥ፥ መተማመንና መተባበር አቅቷቸው፥ ውሉ እንደ ጠፋበት ድር የችግር ቁራኛና ሰለባዎች ከመሆን አልዳኑም። ሥልጣን የጨበጡት ሁሉ ዓይን-አውጣ ውሸታሞችና አጭበርባሪዎች በመሆናቸው፥ በሕዝብ ዘንድ ተአመኔታን አልማግኘት ብቻ ሳይሆን የተጠሉ፥ የተዋረዱና የተናቁ ሆነዋል። በሕዝብ ፊት የተጠላ፥ የተናቀና የተዋረደ "መንግሥት" ደግሞ፥ የቱን ያህል ሥልጣኑ መኅበረሰባዊ መሠረት እንደሌለው የታወቀ ነገር ነው። ወያኔዎቹ፥ ዛሬ እኳንስ የመላውን የኢትየጵያን ሕዝብ ቀርቶ፥ ነፃ እውጥተነሃል ያሉትን የትግራይን ሕዝብ ልባዊ ድጋፍ ማግኘታቸውንም የሚጠራጠሩ ሆነዋል።*

*ተደጋግሞ ተደጋግሞ እንደሚነገረው ከሆነ፥ ኢትዮጵያ በተለያየ ሙያ የተካኑ የሰለጠኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድረው ከፍኛውን ደረጃ የያዙ እጅግ ብዛት ያላቸው ምሁራን እንዳሉ ይታወቃል። እንደ ጨው ዘር በዓለም ዙሪያ የተበተነው ምሁር በዓይነትም፥ በጥራትም ሆነ በብዛት ሲታይ የአፍሪካን ሀገሮች በዕጥፍ ድርብርብ እንደሚያስከነዳ የሚናገሩ ሰዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።ይህ ሁሉ የሰሠለጠነ፥ የደለበና ዕምቅ የሰው ኃይል ፥ የባዕድ ሀገሮችን እያገለገል እያለ፥ በአንድ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ የመጨረሻውን የኑሮ ደረጃ ይዛ ስትገኝ፥ ይህ እንቆቅልሽ፥ አዚምና የታሪክ ምፀት ምን እንደሆነ ለመረዳት ያስቸግራል። ሀገራችን የችግሯ ገመድ ሊበጠስ ያልቻለውና መፍተሄ ማግኘቱ ቀርቶ፥ገና የችግሯን ማንነት እንኳ በጥልቀት ለመራድ ያልተቻለበትን ምክንያት ለማወቅ ተችሏል ማለት ያስቸግራል። እስከ አሁን!*

*ቻይና ፥ደቡብ ኮሪያና ሕንድ በአርአያነት ከሚጠቀስበት አንዱ፥ በውጭ ሀገሮች ያሏቸው ምሁራን በሀገራቸው ግንባታ ላይ የሚጫወቱት ማዕከላዊና ወሳኝ ሚና ነው። የሚገርመው ደግሞ፥ እነዚህ ለአብነት የተጠቀሱት ሦስት ሀገሮች በአጭር ጊዜ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ የደረሱት፥ የቆየ ባህላቸውን ዕምነታቸውን፥ ታሪካቸውንና ሥነ-ምግባራቸውንም ሆነ ብሔራዊ ማንነታቸውን ሳይበርዙ እንደጠበቁ ነው። "ሳይከካ ተቦካ" እንደሚባለው ይትበኃል፥ እኛ ምኑንም ሳንይዘው ሀገርንና ታሪክን ሊያጠፋ በሚችል ነገር ላይ እናተኩራለን። ሀገር ጠፋ፥ ታሪክ ወደመ፥ ሊባል የሚቻለው እኮ ተተኪውን ትውልድ የአልባሌ ባህል ሰለባ ሲደረግ ነው።ታዲያ በዚህ እረገድ ወያኔ ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱ ያለምክንያት አይደለም። ተተኪን ትውልድ መበከል ማለት፥ ነገ ኢትየዮጵያ እንደ ሀገር ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዳይቀጥሉና እንደይኖሩ ማድረግ ማለት ነው። የሠለጠነ ኃይል አለ ማለት፥ በሳይንስ፥ በቴክኖሎጂና በዕደ -ጥበብ መራቀቅ ብቻ ሳይሆን፥ የሀገርን ሁለንተናዊ ችግር ተረድቶ መፍተሄ ማግኘትንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው ። ይህ እስካሁን በሀገራችን ተከስቷል ብለን ለመናገር የምንቸገር ይመስለናል። የኢትዮጵያን ብሔራዊ ችግሮች የማስወገድ ኃላፊነት ደግሞ፥ በተቃዋሚ ድርጅቶች ጫንቃ ብቻ የሚተው አይደለም። የኢትዮጵያ ምሁራን የሚጫወቱት መሠረታው ሚና እንዳለቸውም ሕዝቡ የሚጠብቀው ነው። እነርሱም ቢሆኑ ይህንን ይዘነጉታል ማለት አይቻልም።*

የምሁራን ፍልሰት የአዕምሮ ንጥፈት( Brain-Drain) በሀገራችን መከሰት የጀመረው በዘመነ ደርግ መሆኑ ባያከራክርም፥በብዛት ሀገሩን እየለቀቀ እንዲሰደድ የሚደረገው ግን ፀረ-ሀገርና ፀረ- ልማት በሆነው በወያኔ ዘመነ-መርገም ነው። የአንድን ሀገር ሕዝብ ከታላቅ ድኀነት አላቅቀው ለኢኮኖሚ ዕድገት ከሚያበቁት መካከል፥ የዚያች ሀገር የተፈጥሮ ኃብትና የአየር ጠባይ፥ የሕዝቡ ሥራ ወዳድነትና ታታሪነት፥ እንዲሁም የሰለጠነ የሰው ጉልብት/ ኃይል በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው። እነኝህን ሁሉ ኢትዮጵያ የተነፈገች አይደለችም። ያም ሆኖ ግን፥ የሰለጠነው የሰው ኃይል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የሚጠበቅበትን ሁሉ አሟልቷል ግዴታውን ተወጥቷል ማለት አንችልም። የፖሊቲካው ሥርዓት ያስከተለው ተፅዕኖና አንደምታ ብሎም ያመጠው አሉታዊ ውጤት በቀላሉ የሚገመት ሆኖ አልተገኘም። የተማረው የሰው ኃይል አገሩንና ያስተማረውንም ሕዝብ ለማገልገል፥ ሀገሪቱ የአልቻለበት ሁኔታ በቂ ምክንያትና ማጠየቂያ አለው ለማለት ቢቻልም፥ እናም ደግሞ፥ ሕዝቡን ለማገልገል ባለመቻሉ የሞራልና የመንፈስ ቆርቋሬ ሊኖረው ቢችልም፤ ዞሮ ዞሮ ተጎጅዎቹ ሀገሪቱና ዜጎቿ ናቸው። በተለይም የገጠሩ ነዋሪ! ምሁሩ፥ በግል ደረጃ በኑሮው ሊጎዳ የሚችል የኅብረሰብ ክፍል አይደለም። ሌላው ቢቀር በሀገሩ ውስጥ ለመኖር ባይችልም እንኳ በመላው ዓለም ተሰድዶ በሙያው ሰርቶ የመኖር ዕድሉ የመነመነ አይደለም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ሞልቶ- ተርፎት፥ ነገር ግን አንዱንም ሳያገኝ የበይ ተመልካች በመሆን በችግር ይማቅቃል። ሁሉንም ነገር ባያጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ነገር ባለማግኘቱ ፥ "ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ" እየለ ይኖራል። በዕርግጥ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመፍታት ምሁሩ የሚጫወተው ሚና ወሳኝነት ቢኖረውምው፥ የዘር ፖሊቲካ ባስከተለው ሰበብ ልክ እንደማንኛውም ዜጋ ሀገሩን እየለቀቀ ለመሄድ ተገድዷል። ይህንን ሁሉም ዜጋ ሊረዳለት ይቻላል። ያም ሆነ ግን እንኳን ከወያኔ ተላቀቅሁ በሎ ብቻ ሀገሪቱ ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ መዘንጋት ግን አይጠበቅበትም። በዓለም የተሰራጨው ምሁርና የሰለጠነው የሰው ኃይል፥ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን ኃላፊነትም ግዴታም እንዳለው ዘንግቶታል ለማለት አይቻልም ። አስተምሮ ለዚህ ያበቃው የደሀ ገበሪና የሠረተኛም ዕዳ እንዳለበትም ይገነዘበዋል ለማለት እንወዳለን። ሁሉም የተማረ ዜጋ የአስተማረውን ሕዝብ ዕዳ ሊከፍል ይገባዋል። ዕዳውን ያልከፈለና አደራውን የበላ ዜጋ ደግሞ እንደ ቀማኛና ሸፍጠኛ ሊቆጠር ይችላል። ይህም ከተተኪው ትውልድና ከታሪክ ወቀሳ ነፃ አያደርግም። በዓላማቸው ፀንተው የሚታገሉትን ድርጅቶችንም መደገፍ፥ መርዳና ሲሳሳቱም ምሁራዊ ምክርና ተግሳፅ እንዲያቀርብባቸው ይገባል። ይህ ደግሞ ከህሊና ወቀሳ ነፃ የወጣ ምሁርና የሞራል ሥልጣን አለኝ ብሎ በንፁህ ኅሊናው ከሚተማመን መለካም ዜጋ የሚጠበቅ ፀጋ ነው ብለን እንገምታለን። የኅሌናው ተገዥ የሆነና አዕምሮውን ለማንም/ ለምንም የማያስገዛ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይህንን ከመፈፀም ሊያመነታ አይገበውም እንላለን። ለመኖር ብቻ ሲባል የሚኖረው ኑሮ ደግሞ ካለመኖር የሚቆጠር ይመስለናል። በመኖርና ባለመኖር መካከል ያለው ልዩነት፥በመሞትና በሕይወት በመኖር መካከል እንዳለው

ልዩነት ብቻ አይደለም:: እየኖሩ በመሞትና እየሞቱ በመኖር መካከል ያለው ልዩነት ጭምር ነው::

የኢትዮጵያ ምሁራን፥ በዜግነታቸውም እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ ስለ ሀገራቸውና ስለ ሕዝባቸው ችግር እንደሚያዝኑ፥ እንደሚቆረቆሩና እንደሚበሳጩ ማንም ሊጠራጠር አይችልም:: መፍትሄ ፈልጎ ሀገርን ከጥፋት ለማዳን ከማነኛውም ዜጋ በበለጠ የተለየ ኃላፊነት እንደሚጠበቅባቸው ግን ሊረዱት ይገባል የሚል ፅኑ ዕምነት አለ:: ከአልተማረው ዜጋ ሊለያቸው ይሚችለው ደግሞ ሀገር ታማ ስትጣጣር መዳኀኒት ማግኘትና ከሞት አፋፍ ማዳን ሲችሉ ብቻ ነው::

ወያኔ እውነተኛ ሀገር ወዳድ ምሁራንን እያጠፋ፥ በቦታቸው ለእርሱ ዓላማና ፖሊሲ ታማኝና አገልጋይ የሆኑትን አሳፋሪ ግለሰቦች እየተካ ይገኛል:: ይህ ሂደት ወያኔ ምንሊክ ግቢ እሰካለ ድረስ ይቀጥላል:: ምናልባትም ይህ ክስተት ወያኔ ኢትዮጵያን አጥፍቶ እስከሚጠፋ ድረስ ሊቀጥል ይችላል ብለው ስጋታቸውን የሚገልጹ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በቀላል የሚገት አልሆነም:: ለዚህ ስጋትና ጭንቀት መድኃኒቱ አንድ ብቻ ነው:: ሁሉም ሀገር ወዳድ ዜጋ፥ በኅብረት በመነሳት፥"ክተት መክት" ብሎ ወያኔንና ዘረኛ ሥርዓቱን፥ ለውጦ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መመሥረት ነው:: ይህ ደግሞ ምኞት ሳይሆን በዕርግጥም የሚሆንና የሚሳካ፥ የነፃነትን ፋናን ጨብጦ የሚመጣ የታሪክ ሀቅ ነው:: ዘረኛው የአምባገን ሥርዓት፥ ከእርሱ በፊት እንደነበረው ፋሽስታዊ ወታደራዊ ደርግ ወደ ከርሰ- መቃብሩ እንደሚወርድ የኢትየጵያ ሕዝብ አንዳችም ብዥታ የለውም::